የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር

ETHIOPIAN PEOPLE PATRIOTIC FRONT

# በኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ስም ህዝብን ማሳሳትና መነገድ ይቁም !

ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የተሰጠ መግለጫ

ቀን መስከረም 14/2009 ዓ.ም

ሃገራችን ኢትዮጵያ በወያኔ ኢሃዴግ ጋሻ ጃግሬዎችና ለሆዳቸው ባደሩ ሎሌዎች የበላይነት ለበርካታ ዓመታት ለህዝባቸው ነጻነት የቆሙ ወድ ታጋይ ልጆቿን እየገበረች በምትገኝበት በዚህ ወቅት ለሃገሩ ለህዝቡና ለወገኑ ያልቆመ ቢኖር ሃገሩን አሳልፎ የሸጠ ባንዳ ነው።

ግንቦት 7 የተባለው ድርጅት በሃገራችን ጉዳይ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን ስም በማጉደፍና ለትግሉ ጋሪጣ በመሆን በድርጅታችን ወስጥ ያሉትን ታጋይና ቆራጥ አባላትን በመደለል ሁለተኛ ጥፋቱን ጀምሯል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ከዚሁ ተጠቃሽ የግንቦት 7 ድርጅት ጋር ያደረገው ወህደት ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ያላደረገና ጭራሹኑ የሃገራችን ሕዝብ የሚያደርገውን ተጋድሎ ያዳፈነና ለትግሉ ተጠቃሽ ጋሬጣ ሆኖ ይገኛል።

ውድ በሃገር ወስጥና በውጪው ዓለም የምትገኙ እንዲሁም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የትግሉ አካል የሆናችሁ ወገኖች “ ላም ባልዋለችበት ኩበት ለቀማ እንዲሉ” እጅግ ወድ በሆነ የቤት ኪራይ በቁጥር ሶስት የሚሆኑ በአስመራ የሚገኙት የግንቦት 7 ከፍተኛ አመራር አካላት ለተጠየቁት ወቅታዊ ጥያቄ ምላሽ ከሰራዊቱ ጋር ዕለታዊ ግንኙነት አለን ፣ሕብረት አለን ፣እንዲሁም በመሬት ላይ እንቅስቃሴ እያደረግን ነው በማለት የሚያወሩትና የሚያስወሩት ከእውነት የራቀ መሆኑን እናስገነዝባለን።

ይልቁንም በውህደቱ ስም ከዲያስፖራው የተሰበሰበው ገንዘብ በጥቂት የግንቦት7 አመራሮች ፈላጭ ቆራጭነት በየሆቴሉና መዝናኛ በታዎች እየተበተነ ይገኛል።

ለሰራዊቱ ከዓመት በፊት ከተሰጠው የተስፋ ፕሮፖጋንዳ ወጪ አንድም ነገር የደረሰው የለም፣ ከአውሮፓና አሜሪካ ሽሽግ ጉዞና መልሳቸው አስመራ ከተማ በተገኙበት ወቅት ተጠይቀውም የሰጡት በጎ ምላሽ የለም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር EPPF ኢ.ሕ.አ.ግ.

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር

ETHIOPIAN PEOPLE PATRIOTIC FRONT

በአሁን ሰዓት የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር መሬት ላይ እያደረገ ያለውን ተግባራዊ እንቅስቃሴ በስዕልና ድምጽ በታገዘ ዘገባ ለአባላቶቻችንና ደጋፊዎቻችን የሕዝቡ አሌኝታነትና ድጋፍን ጨምሮ ይፋ የሚሆንበት ጊዜ እሩቅ አይደለም(አሁን ያልተደረገበት ምክናየት ወታደራዊ ሚስጥራዊነቱን ለመጠበቅ ብቻ መሆኑን እንገልጻለን)።

በመሆኑም የግንቦት 7 ጥቂት አመራር አካላት ለነጻነት በቆሙ በውጪ የሚገኙ አባላትና ደጋፊዎች ትብብር ከቤተሰቦቻቸው ጉሮሮ እየነጠቁ የተሰበሰበውን ገንዘብ ለትግሉ በግንባር እንዲያስረክቡ እየጠየቅን ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ስም ሕዝብን ማሳሳትና መነገድ ይቁም መልዕክታችን እንዲከበር እናስገነዝባለን ።

በተጨማሪም ይህንን እና መሰል ትግልን የሚያኮላሹ በሃገር ውስጥና በውጪ ሃገራት የሚደረጉትን የትግል እንቅስቃሴዎች እኛ እንምራው ፣እናፍነው፣እንቆጣጠረው፣ከእኛ ውጪ ለሃገር የቆመ የለም በማለት የህዝብን ትግል ተመርኩዞ ባቋራጭ ስልጣን ለመያዝ የሚደረግ እሩጫ የመሳሰሉ ግመኛ አካሄዶችን አጥብቀን እንቃወማለን እንታገላቸዋለንም ።

በተጨማሪም ግንቦት 7 በተባለው ድርጅት ወስጥ በዓባልነትና ደጋፊነት የድርጅቱን አፍራሽ አካሄድ ያልተረዳችሁ ቆም ብላችሁ በማሰብ ሁኔታዎችን እንድትመለከቱ እናስገነዝባለን!!

በታጋዩ ስም መነገድ ይቁም !!

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር

አንድነት ሃይል ነው!!